# <u>የተነፋችው ፊሽካ የት ደረሰች!</u>

ፕረዚደንት ኦባማ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ በአጋጣሚ ይሁን ሌላ ሚስጥር ይኑሮው በውል ባይታወቅም አንድ የተገጣጠመ ነገር ነበር፤ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ አስመራ መግባት። ይህን አስመልክቶ አንድ ጽሑፍ አንብቤ ነበር። ጽሑፍዋም " የታደለው ኦባማን ያሰተናግዳል ያልታደለው ብርሃኑን ይቀበላል" የምትል ነበረች።
የዶክተሩና ተከታዮቻቸው አስመራ መመሸግ አስመልክቶ የተለያዩ አሰተያየቶች ሲሰነዘሩ ሰንብተዋል፤ አሁንም እየቀጠሉ ናቸው። በተለይ ደምስ በለጠ ያነሳት ውሐ የምታነሳ ሁና አግኝቻታለሁ። ምነው አርበኛው ከአሜሪካ ብቻ ሆነ፤ ከአውሮፓና ከኤስያ ወኔ ያለው ጠፍቶ ነው ወይስ ምክንያቱ ሌላ ነው። ደምስ እንደጠረጠረው ሁላችንም መጠርጠር የግድ ይላል። ምናልባት ተነቃብን ብለው አንድ ሁለት እንኳን ጣል ቢያደርጉ አሁንም መጠርጠር። ጥርጣሬው ጥርጣሬ ብቻ ሆኖ እንዲቀር የሚያደርገው የተከበሩ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ አቶ ነአምንና አቶ ኤፍርምን አስከትለው እዚሁ ቨርጂንያ ሸራተን ሆቴል በፓወር ፖይንተ እየተጠቀሙ በስክሪን ስለሚባለው ጉንቦት 7 አርበኞች ጦር መግለጫ ሲሰጡ ብቻና ብቻ ነው። ሞኝህን ፈልግ እስካላሉ ድረስ።
ይኸኛው በዚህ ይብቃኝና አቶ ኤፍሬም ማዴቦ " ከዊሃ እስከ ኦምሃጀር- አንድ ሰሞን ከአርበኞች ጋር" የሚል ጹሑፍ አስነብበውናል። በጽሑፋቸው <u>*ቨርጂንያ ከሚገኘው ዳላስ አየር ማረፊያ*</u> ጀምረው <u>*አስመራ ከሚገኘው አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ*</u> እስከደረሱበት የነበረው ጉዞ በሚጣፍጥ አማርኛ አውግተውናል። በነገራችን ላይ የአስመራው አለም አቀፍ የሚል መዓርግ ሲሰጡት ምነው የቨርጂንያው ነፈጉት ወይስ በሳቸው መመዘኛ አለም አቀፍ ለመባል አልደረሰም ወይ?
ሌላው "አርበኞቹ" አሉበት የተባለው ስፍራ ለመድረስ ግሩም በሆነ የስእላዊ ድርሰት አጻጻፍ ስልት ተርከውልናል። የተራራው ርዝመት፡ አንዱ ባንዱ የመደራረብ ጉዳይ በጣም አድካሚና እልህ አስጨራሽ እንደሆነ፤ እንደሳቸውና እንደ ጓዶቻቸው የቆረጠና የተሟላ ወኔ ያለው ካልሆነ ምንም ሊደፍረው እንደማይችል ነግረውናል። አዎ የኤርትራ ቆላማ አከባቢዎች እንደዛ ናቸው በትክክል ተገንዝበውታል። የጠቀስዋቸው አስቸጋሪ ቦታዎች የኤርትራ ታጋዮች መሸገውባቸው የነበሩ ናቸው። እነሱ እዚህ ቦታ ላይ ሲመሽጉ ወደው ሳይሆን የደርግ ሰራዊት ዋና ዋና የሚባሉ ገዢ መሬቶች ይዞዋቸው ስለነበረ እንጂ የግድ እዛ ቦታ መኖር ተመርጦ አይደለም።አሁን ግን ኤርትራ ነጻ ሃገር ናት፤ ደጋውም ቆላውም በኤርትራ መንግስት ቁጥጥር ስር ነው። አቶ ኤፍሬም በመጀመሪያ እግራቸው ያልተገነዘቡትና በትረካቸው ያላካተቱት በአሁኑ ጊዜ እውን አቶ ኤፍሬም እንደገለጹት በእንደዚህ ያለ የመሬት ላይ ገሃነም መኖር አስፈላጊ ነው ወይ?
አቶ ኤፍሬም አንዳንድ ጋዜጠኞች የዳውን ታውን ቅምጥሎች በማለት ተችተዋል። ይህ ስም እነ ዶክተር ብርሃኑ ሲጠሩበት የነበረ ነውና ከዚህ ስያሜ መላቀቃቸው እንኳን ደስያላችሁ እላለሁ።
ዋናው ጉዳይ አቶ ኤፍሬም አርበኞች መንደር ያሉት ሲደርሱ ግልጽ ያደረጉት ጉዳይ ቢኖር የተለያዩ ካምፖች መገንዘባቸውን፤ እነዚህም ለየግላቸው እንጂ ምንም አንድነት እንደሌላቸው፤ እና " አንድነት ስለሌለን እባካችሁ ገላግሉን" እንዳሏቸው የገለጹት ትልቅ መልእክት የሚያሰተላልፍ ነው። በነገራችን ላይ አቶ አንዳርጋቸው

በወያኔ ሲያዙ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የተናገሩት ነበር። አቶ አንዳርጋቸው በኤርትራ በረሃ የነበረውን ስራ ጨርሰዋል ነበር። ታድያ የአቶ አንዳርጋቸው ቁልፍ ስራ የየራሳቸው ድንኳን ተክለው በጎሪጥ እንዲተያዩ ነበር ወይ፤ አሁን አንድ የማድረግ ጉዳይ እንደአዲስ ለአቶ ኤፍሬም ጥያቄ የሚቀርብላቸው? እነዛ ዋሾ ወሬኞች የተባሉት ጋዜጠኞች ከዚህ በላይ ምን ተናገሩ። ለኢትዮጵያ የሚበጅ መፍትሄ ከኤርትራ በረሃ አይገኝም ነው። አንዱ ምክንያታቸው የኢሳያስ መንግስት ትናንሽ ድርጅቶች በመፈልፈል ኢትዮጵያን ማተራመስ እንጂ የተዋሃዱና ጠንካራ የሆኑ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ እንዲፈጠር አይፈልግም ምክንያቱም ጠንካራና አንድነትዋን የጠበቀች አትዮጵያ ለኢሳያስ መንግስት እንደማትበጅ አሁን ካለው ሁኔታ በውል ተገንዝበዋል። ስለዚህ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እነ አቶ ኤፍሬም ምንም ውጤት በሌለው እየዳከሩ መሆናቸውን ከማስገንዘብ ውጭ የከፋ ነገር የጻፉ ወይም የተናገሩ አይመስለኝም።

ሌላው አስገራሚ የዴምሐት አሰፋፈር ነው። እዚህም አቶ ኤፍሬም ሳያስቡት አንድ ትልቅ ሚስጥር አውጥተዋል። እንደሚባለው ከሆነ ዴምሐት ለሸፋን የተሰጠው ስም እንጂ እንደስሙ አይደለም። ዴምሕት ዋና ተልእኮ ፕረዚዴንት ኢሳያስን ከማንኛውም የውስጥ አደጋ መከላከል ነው። ዴምሐት የሚል ስም የተሰጠው ሽፋን ነው። ዴምሐት አንዳንድ ጊዜ ድንገት አስመራ ገብቶ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን የሚይዘው ለምን ይመስላችኋል? አቶ ኢሳያስ ጀርባቸው አንድ ነገር ሲነግራቸው በቅጽበት ከች እንዲል ይደረጋል። ለህዝቡ የሚነገረው ግን ወደፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲገቡ የከተማ ውጊያ ስለሚያጋጥማቸው ለመለማመድ ነው ይባላል። ሌላው የዴምሕት አቀማመጥ ወደ ምጽዋ የተጠጋ ነው፤ የፕረዚዴንቱ ያልታወጀ ዋና ከተማ ምጽዋ መሆንዋ ማጤን አስፈላጊ ነው። ማንም በፕረዚዳንቱ አደጋ ለማድረስ የሚንቀሳቀስ ሃይል የሚያልፈው ዴምሐት በመሸገበት ቦታ ነው። ስለዚህ ያልተፈቀደለት ሃይል ወደ ምጽዋ አከባቢ ቢጠጋ መጀመሪያ የሚጋፈጠው ከዴምሐት ነው። ይህ ሃይል በኤርትራ በረሃ ከመሸጉት ተቃዋሚ ድርጅቶች በቁመናው፤ በትጥቁ፤ በስልጠናው በጣም የተሻለ የሚባል ነው። ይህ የሆነበት ደግሞ ባጋጣሚ ሳይሆን ታስቦበት የተደረገ ነው። የዚህ ሃይል አወቃቀርና የሰው ሃይሉ ስብጥር በተለያየ ጊዜ ኤርትራ ደርሰው የመጡት በዝርዝር ስለገለጹት አሁን መድገም አያስፈልግም።

በመጨረሻ ዶክተር ብርሃኑ አስመራ ሲገቡ የድርጅቱ ቃል አቀባይ የጨዋታው ፌሽካው እንደተነፋ፤ ከእንግዲህ በየቀኑ የድል ዜና መከታተል እንደሚያስፈልግ “ አበስሮ” ሲያበቃ ፊሽካዋ ሓሪና በረሃ አሸዋው ውስጥ ወድቃ ጠፍታ ነው መሰለኝ ዳግም ስትነፋ ለመስማት እድል አላገኘንም።

አሁንም ወቅቱ የሚጠይቀው የትግል ስልት መጠቀም የብልሆችና የአገር ወዳዶች ነው። በሌለ ነገር ስለፈለግከው ወይም ስላልከው ብቻ የሚሳካ ነገር የለም። እውነቱን እንናገር ካልን እንኳንና ያለውን መንግስት ገልብጠህ መንግስትነት መያዝ ይቅርና የደሮዋን ያህል አቅም ብታጠራቅሙም ባልበላውም እበትነዋለሁ እንዳለቻው እንደማይሆንላችሁ ላስረግጥላችሁ እወዳለሁ። ለዚሁ ደግሞ ነብይ መሆን አያሰፈልግም በመሬት ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በቂ ማስረጃ ነው። ምንም እንኳን መሰስተካከል ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ቢኖሩም በዓለማችን ሃያላን የሚባሉት አገራት መሪዎች ቀልብ የሳበችው ያጋጣሚ ወይም ስላሳዘነቻቸው ሳየሆን የወደፊት ቦታዋ ካሁኑ እንቀቅስቃሴዋ ተረድተው ነው። እናንተም እነዚህ

ሃያላን የተጠቀሙበትን መነጸር ተጠቅማችሁ የሚበጀውን ብትወስኑ ለሁሉም ይበጃል ፣ በተለይ ለናንተ።
በመጨረሻ አንድ ነገር ብዬ ላጠቃልል።
አንድ ዓይነ ስውር ትንሽ ይነሽጠውና እሸፍታሁ ብሎ ጓሮ ካለው የበቆሎ ማሳ ይመሽጋል። እንዳይርበው ባይበስልም ከበቆሎው እየሸለቀቀ በመመገብ ለሁለት ቀናት ይቆያል። በልቡ መሸፈቱ አገር ያወቀለት መስሎት ራሱን በራሱ እያንቆለጳጰሰ እያለ የበቆሎ ማሳው ባለቤት ሚስት ለራት የሚሆን የበቆሎ እሸት ለማምጣት ማሳው ውስጥ ስትገባ አይነስውሩን ታገኘውና ደንግጣ አንተ እዚህ ምን ታደርጋለህ ብተለው፣ እሱም  እሱን ተይና ሰው ምን እያለ ነው፣ በመሸፈቱ እየተጨነቀ ነው ወይ አላት። ሴትዮዋም ከት ብላ ስቃ የምን ሽፍቶ ብሎ መጨነቅ፣ ሰዉማ የተጨነቀው ይሄ  ዓይነ ስውር የትኛው ገደል ገብቶ ተሰባብሮ ሞቶ ይሆን እያለ ነው ብላው እርፍ።

ሰላም እንሁን
አበበ ሃይለ